የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፲፩
አዲስ አበባ የካቲት ፴ ቀን ፪ሺ፲፬

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

28th Year No 11
ADDIS ABABA 9th March, 2022

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፬፻፺፪/፪ሺ፲፬

የባለሞተር ተሽከርካሪዎች የፍጥነት ወሰን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.........ገጽ ፲፫ሺ፱፻፷፯

## Content

Regulation No. 492/2022

Motor Vehicles' Speed Limit Council of Ministers Regulation....................Page 13967

## ደንብ ቁጥር ፬፻፺፪/፪ሺ፲፬

## የባለሞተር ተሽከርካሪዎች የፍጥነት ወሰን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር ፬፻፷፰/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፳፰ መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የባለሞተር ተሽከርካሪዎች የፍጥነት ወሰን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፺፪/፪ሺ፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ ፡-

፩/ "አዋጅ" ማለት የትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር ፬፻፷፰/፲፱፻፺፯ ነው፤

፪/ በአዋጁ አንቀጽ ፪ የተሰጡት ትርጓሜዎች እንደአግባቡ ለዚህ ደንብም ተፈጻሚዎች ይሆናሉ፤

## REGULATION No 492 /2022

## MOTOR VEHICLES' SPEED LIMIT COUNCIL OF MINISTERS REGULATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 28 of the Transport Proclamation No. 468/2005.

### PART ONE

### GENERAL PROVISIONS

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Motor Vehicles' Speed Limit Council of Ministers Regulation No 492/2022".

**2. Definitions**

Unless the context requires otherwise in this Regulation:

1/ "Proclamation" means Transport Proclamation No. 468/2005;

2/ the definitions assigned to the terms under Article 2 of the Proclamation shall be applicable to this Regulation;



Scanned by CamScanner

፫/ "የፍጥነት ወሰን" ማለት በማንኛውም ሁኔታ አንድ ባለሞተር ተሽከርካሪ ሊሽከረከርበት የተፈቀደለት ከፍተኛው ፍጥነት ነው፡

፬/ "የከተማ መንገድ" ማለት ዋና የከተማ መንገድ ወይም መለስተኛ የከተማ መንገድ ወይም የሰፈር መንገድ ወይም ቀለበት መንገድ ነው፣

፭/ "ዋና የከተማ መንገድ" ማለት የቀለበት መንገድን ሳይጨምር ዋና አገልግሎቱ ከፍተኛ ብዛት ያለውን ትራፊክ በፍጥነት ማስተናገድ የሆነና መገናኛ ኖሮት አሽከርካሪዎች ረዘም ያለ ርቀት እንዲያሽከረክሩበት ታስቦ የተሰራ መንገድ ነው፤

፮/ "መለስተኛ የከተማ መንገድ" ማለት ደረጃው ከዋና የከተማ መንገድ ያነሰ፣ አገልግሎቱ የትራፊክ እንቅስቃሴን ወደ ተለያየ አቅጣጫ ማከፋፈል የሆነ እና በአጭር ርቀት ውስጥ ከሰብሳቢና ከሰፈር መንገድ ጋር በከፍተኛ ደረጃ ለማገናኘት ተብሎ የተሰራ መንገድ ነው፤

፯/ "የሰፈር መንገድ" ማለት ወደ ሰዎች ይዞታ ወይም ወደ ሰፈር ውስጥ ወይም ሰፈርን አቋርጦ ወደ ዋና ወይም ወደ መለስተኛ የከተማ መንገዶች የሚደረግ የትራፊክ እንቅስቀሴ ለማካሄድ እንዲረዳ ተብሎ የተገነባ መንገድ ነው፤

፰/ "የቀለበት መንገድ" ማለት ዋና አገልግሎቱ የትራፊክ እንቅስቃሴን ፈጣን ማድረግ የሆነ፣ በአንድ አቅጣጫ የውስጥ እና የውጭ መጓጓዣ መንገድ ያለው፣ እግረኛ እንዳያቋርጥ መከለያ ሊኖረው የሚችል፣ ትራፊክ ወደ መሀል ሳይገባ ወደ መዳረሻ እንዲጓዝ የሚያስችል መንገድ ነው፡

፱/ "የከተማ ያልሆነ መንገድ" ማለት አውራ መንገድ ወይም አገናኝ መንገድ ወይም ዋና መዳረሻ መንገድ ወይም ሰብሳቢ መንገድ ወይም መጋቢ መንገድ ነው፡

3/ "Speed Limit" means the maximum speed at which a motor vehicle may be driven in any given situation;

4/ "Municipal Road" means main municipal road or medium municipal road or local road or ring roads;

5/ "Main Municipal Road" means a municipal road in exclusion of a ring road having junctions; and the principal purpose of which is handling high traffic with the higher speed limit for a longer route;

6/ "Medium Municipal Road" means any municipal road lesser in grades from main municipal road and having short range junctions and higher connectivity with local and collector roads; and the principal purpose of which is handling traffic flowing to several directions;

7/ "Local Road" means road the principal purpose of which is routing to dead-ends or localities; or passing through localities; or connecting to medium municipal road;

8/ "Ring Road" means road the principal purpose of which is handling high speed limit traffic having both non-exit and exit lanes in each opposing direction with possible barriers to pedestrians; and serving uninterrupted traffic;

9/ "Non-Municipal Road" means trunk road or linking road or main access road or collector road or feeder road;

Scanned by CamScanner

፲/ "አውራ መንገድ" ማለት ከፌደራል መንግሥት ዋና ከተማ ተነስቶ የተለያዩ የክልል ከተሞች የሚያቋርጥ ወይም ጎረቤት ሀገሮችን የሚያገናኝ መንገድ ነው፣

፲፩/ "አገናኝ መንገድ" ማለት የሀገራችንን አውራ መንገዶች የሚያገናኝ መንገድ ነው፣

፲፪/ "ዋና መዳረሻ መንገድ" ማለት ከተለያዩ ቦታዎች በመነሳት ወደ አገናኝ መንገድ የሚያገናኝ መንገድ ነው፣

፲፫/ "ሰብሳቢ መንገድ" ማለት ዋና መዳረሻ መንገዶችን የሚያገናኝ መንገድ ነው፣

፲፬/ "መጋቢ መንገድ" ማለት ሰብሳቢ መንገዶችን የሚያገናኝ መንገድ ነው፣

፲፭/ "የፍጥነት መንገድ" ማለት በሁለት ተቃራኒ አቅጣጫዎች ሁለትና ከሁለት በላይ የትራፊክ ፍሰትን በተመሳሳይ አቅጣጫ ለማስተናገድ የሚያስችል ረድፍ ያለው መንገድ ሆኖ በመንገዶቹ መግቢያና መውጫ ቁጥጥር የሚደረግበት ለፍጥነት ታስቦ የተዘጋጀ የታጠረ መንገድ ነው፣

፲፮/ "ደረጃ አንድ መንገድ" ማለት በቀን ከ፲ሺ /አስር ሺህ/ በላይ የተሽከርካሪ የትራፊክ እንቅስቃሴ ለማስተናገድ እንዲችል ታስቦ የተሰራ አስፋልት የሆነ አውራ መንገድ ነው፣

፲፯/ "ደረጃ ሁለት መንገድ" ማለት በቀን ከ፫ሺ/ሦስት ሺህ/ በላይ እና እስከ ፲ሺ/አስር ሺህ/ የተሽከርካሪ የትራፊክ እንቅስቃሴ ለማስተናገድ እንዲችል ታስቦ የተሰራ አስፋልት የሆነ አውራ መንገድ ወይም አገናኝ መንገድ ነው፣

10/ "Trunk Road" means an asphalt road that arises from the Capital City of the Federal Government and passes through the cities of Regional States or connects with neighboring countries;

11/ "Linking Road" means a road linking trunk roads of the country;

12/ "Main Access Road" means a road that originates from different places and connects to linking road;

13/ "Collector Road" means a road that connects main access roads;

14/ "Feeder Road" means a road that connects collector roads;

15/ "Express Road" means a trunk road with two or more lanes in each opposing traffic direction; and built with the principal purpose of handling high speed traffic having a control system at the entrance and exit points;

16/ "Level One Road" means a trunk road constructed with the purpose of handling a daily traffic of more than 10,000 /Ten Thousand/ motor vehicles;

17/ "Level Two Road" means a trunk or a linking road constructed with the purpose of handling a daily traffic of more than 3,000 /Three Thousand/ and up to 10,000 /Ten Thousand/ motor vehicles;

Scanned by CamScanner

፲፰/ “ደረጃ ሶስት መንገድ” ማለት በቀን ከ፩ሺ /አንድ ሺህ/ በላይ እና እስከ ፫ሺ/ሦስት ሺህ/ የተሽከርካሪ የትራፊክ እንቅስቃሴ ለማስተናገድ እንዲችል ታስቦ የተሰራ አስፋልት የሆነ አውራ መንገድ ወይም አገናኝ ወይም ዋና መዳረሻ መንገድ ነው፤

፲፱/ “ደረጃ አራት መንገድ” ማለት በቀን ከ፫፻ /ሦስት መቶ/ በላይ እና እስከ ፩ሺ /አንድ ሺህ/ የተሽከርካሪ የትራፊክ እንቅስቃሴ ለማስተናገድ እንዲያስችል ታስቦ የተሰራ አስፋልት የሆነ አውራ ወይም አገናኝ ወይም ዋና መዳረሻ መንገድ ነው፤

፳/ “ደረጃ አምስት መንገድ” ማለት በቀን ከ፩፻፶ /አንድ መቶ ሃምሣ/ በላይ እና እስከ ፫፻ /ሦስት መቶ/ የተሽከርካሪ የትራፊክ እንቅስቃሴ ለማስተናገድ እንዲችል ታስቦ የተሰራ አስፋልት ወይም ጠጠር የሆነ አውራ ወይም አገናኝ ወይም ዋና መዳረሻ ወይም ሰብሳቢ መንገድ ነው፤

፳፩/ “ደረጃ ስድስት መንገድ” ማለት በቀን ከ፸፮ /ሰባ ስድስት/ እስከ ፩፻፶ /አንድ መቶ ሃምሣ/ የተሽከርካሪ የትራፊክ እንቅስቃሴ ለማስተናገድ እንዲችል ታስቦ የተሰራ አስፋልት ወይም ጠጠር የሆነ አገናኝ ወይም ዋና መዳረሻ ወይም ሰብሳቢ ወይም መጋቢ መንገድ ነው፤

፳፪/ “ደረጃ ሰባት መንገድ“ ማለት በቀን ከ፳፮ /ሃያ ስድስት/ እስከ ፸፭ /ሰባ አምስት/ የተሽከርካሪ የትራፊክ እንቅስቃሴ ለማስተናገድ እንዲችል ታስቦ የተሰራ አስፋልት ወይም ጠጠር የሆነ ዋና መዳረሻ ወይም ሰብሳቢ ወይም መጋቢ መንገድ ነው፤

18/ “Level Three Road” means a trunk or a linking or a main access road constructed with the purpose of handling daily traffic of more than 1,000 /One Thousand/ and up to 3,000 /Three Thousand/ motor vehicles;

19/ “Level Four Road” means a trunk or a linking or a main access road constructed with the purpose of handling daily traffic of more than 300 /Three Hundred/ and up to 1,000 /One Thousand/ motor vehicles;

20/ “Level Five Road” means a trunk or a linking or a main access road which may be non-asphalt and constructed with the purpose of handling a daily traffic of more than 150 /One Hundred and Fifty/ and up to 300 /Three Hundred/ motor vehicles;

21/ “Level Six Road” means a linking or a main access or a collector or a feeder road which may be non-asphalt and constructed with the purpose of handling a daily traffic from 76 /Seventy Six/ and up to 150 /One Hundred and Fifty/ motor vehicles;

22/ “Level Seven Road” means a main access road or a collector or a feeder road which may be non-asphalt and constructed with the purpose of handling a daily traffic from 26 /Twenty six/ and up to 75 /Seventy five/ motor vehicles;

Scanned by CamScanner

፳፫/ "ደረጃ ስምንት መንገድ" ማለት በቀን ከ ፩ /አንድ/ እስከ ፳፭ /ሃያ አምስት/ የተሽከርካሪ የትራፊክ እንቅስቃሴ ለማስተናገድ እንዲችል ታስቦ የተሰራ ጠጠር የሆነ መጋቢ መንገድ ነው፤

፳፬/ "የግል ተሽከርካሪ" ማለት አሽከርካሪውን ጨምሮ እስከ አስራ ሁለት (፲፪) መቀመጫ ያለው ወይም እስከ ፩ሺ /አንድ ሺህ/ ኪሎ ግራም ወይም ድርብ ተግባር (አራት ሰውና ፯፻፶ ኪሎ ግራም) የሚጭን ማንኛውም የንግድ ያልሆነ ጎታች (ተሳቢ) የሌለው ተሽከርካሪ ነው፤

፳፭/ "ሞተር ብስክሌት" ማለት የጎን ተሽከርካሪውን ሳይጨምር ክብደቱ ከ ፬፻ (አራት መቶ) ኪሎ ግራም የማይበልጥ ከሶስት እግር በታች ያለው ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፤

፳፮/ "ባለ ሦስት እግር ተሽከርካሪ" ማለት ማንኛውም ባለሦሥት እግር ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፤

፳፯/ "የንግድ ተሽከርካሪ" ማለት በኪራይ፤ በጥቅም ወይም ለትርፍ ዓላማ መንገደኞችን፤ መልዕክቶችን ወይም ዕቃዎችን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን እነዚህን የሚያጓጉዝ ባለሞተር ተሽከርካሪ ሲሆን ሞተር ብስክሌት እና ባለሶስት እግር ባለሞተር ተሽከርካሪን ይጨምራል፤

፳፰/ "የአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪ" ማለት የአደጋ አገልግሎት ተግባርን ለመፈጸም በሚዘዋወርበት ወቅት በግንባሩ አቅጣጫ ሳያቋርጥ ብልጭ ብልጭ የሚል ቀይ ወይም ሰማያዊ የመብራት ምልክት የሚያሳይ ወይም ለማስጠንቀቂያ ተስማሚ የሆነ ድምጽ የሚያሰማ አምቡላንስ፣ የመከላከያ ፣ የፖሊስ ፣የደህንነት ወይም የእሳት አደጋ መከላከያ ተሽከርካሪ ነው፣

23/ "Level Eight Road" means a feeder road constructed with the purpose of handling a daily traffic of up to 25 /Twenty Five/ motor vehicles;

24/ "Private Vehicle" means any vehicle with seating capacity of up to twelve including the driver or with a payload capacity of 1,000(One Thousand) kg; or for dual purpose vehicles with four seating capacity and payload capacity of 750 kg; and not registered as commercial purpose vehicle having no trailer;

25/ "Motor Bicycle" means any motor vehicle with loading capacity of not exceeding 400 kg in exclusion of the side locomotive; and having less than three wheels;

26/ "Three Wheel Motorcycles" means any motor vehicle with three wheels;

27/ "Commercial Vehicle" means any motor vehicle registered for commercial purpose and transporting passengers, cargo or parcels or any two or more of these for gain through rent, consideration or profit;

28/ "Emergency Service Vehicle" means an ambulance, a vehicle belonging to or serving with the defense forces, the security, the police or a vehicle designed and used for firefighting, on condition that is traveling in the performance of its emergency duties and is identified by an intermittent red or blue light emitted towards the front or by audible warning signals lauding through a siren or a bell;

Scanned by CamScanner

፳፱/ "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፴/ "አግባብነት ያለው አካል" ማለት የዚህ ደንብ አፈጻጸም የሚመለከተው ማንኛውም አካል ነው፤

፴፩/ "የሚመለከተው አካል" ማለት መንገድን ለመገንባት፣ ደረጃ ለማውጣት፣ ለመጠገን እና ለማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው አካል ነው፤

፴፪/ "ሕገ-መንግሥት" ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት ነው፤

፴፫/ በዚህ ደንብ በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ያጠቃልላል::

## ፫. ዓላማ

የዚህ ደንብ ዓላማ በመንገዶች ላይ የባለሞተር ተሽከርካሪዎችን ከፍተኛ ፍጥነት መወሰን እና በፍጥነት ምክንያት ሊደርስ የሚችልን የትራፊክ አደጋ መቀነስ ነው::

## ፬. የተፈጻሚነት ወሰን

በሕገ-መንግሥቱ ለክልሎች የተሰጠው ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ:-

፩/ ይህ ደንብ በማናቸውም በኢትዮጵያ መንገዶች በሚሽከረከሩ ባለሞተር ተሽከርካሪዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች በአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪዎች ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም::

29/ "Minister" or "Ministry" means the Minister or Ministry of Transport and Logistics, respectively.

30/ "Appropriate Organ" means any organ responsible for the enforcement of the provisions of this Regulation;

31/ "Concerned Organ" means an organ with the authority to construct, set standard, maintain and administer roads;

32/ "Constitution" means the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

33/ Any expression in masculine gender includes feminine.

## 3. Objectives

The objectives of this Regulation are to determine the maximum permissible speed limits of motor vehicles and minimize speed induced traffic accidents.

## 4. Scope of Application

Without prejudice to the powers and duties of Regions as provided in the Constitution:

1/ This Regulation shall be applicable to any motor vehicle operated on any road in Ethiopia;

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the provisions of this Regulation shall not be applicable to emergency service vehicles.

Scanned by CamScanner

## ክፍል ሁለት

## ስለ ፍጥነት ወሰን

### ፭. መሰረታዊ የጥንቃቄ ተግባሮች

፩/ ማንኛውም አሽከርካሪ አደጋን ሳያስከትል ሊያሽከረክር የሚችልበት ሁኔታ መኖሩን በሚገባ አመዛዝኖ ካልሆነ በስተቀር በማንኛውም መንገድ ላይ ባለሞተር ተሽከርካሪን በከፍተኛ ፍጥነት ማሽከርከር የለበትም፡፡ እነዚህ ሁኔታዎችም በዚህ ብቻ ሳይወሰኑ የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፡-

ሀ) የመንገዱ ንጣፍ ስፋትና ጠቅላላ ሁኔታ፤

ለ) መንገዱ የሚያልፍበትን የመሬት ሁኔታ እና በዚህ ምክንያት የሚገጥመውን የመንገድ መጠምዘዝና የመንገዱን ስፋት መጠን፤

ሐ) የዝናብ፣ የጭጋግ፣ የሌሊት ጉዞ ወይም ሌላ የተፈጥሮ ሁኔታ መኖርና ይህ ሁኔታ እይታንና መንዳትን እንዴት እንደሚያውክ፤

መ) በአካባቢው ያለው የነዋሪው ህዝብ መጠን፤

ሠ) ያለው ወይም ይኖራል ተብሎ የሚገመተው የትራፊክ ብዛት መጠን፤

ረ) መዞሪያዎች፣ የተዘጉ መተላለፊያዎች፣ የተሰናከሉ ተሽከርካሪዎች፣ የወደቀ አለት ወይም መተላለፍን የሚያውክ ሌላ መሰናክል መኖሩን፤ እና

ሰ) አሽከርካሪው በማንኛውም ጊዜ ተሽከርካሪውን ሙሉ በሙሉ እንዳይቆጣጠርና አደጋን ሊያደርስ በሚችል አኳኋን እንዳይነዳ የሚያውክ ማንኛውም ሁኔታ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለማንኛውም አሽከርካሪ በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፮፣ ፯ ወይም ፰ የተመደበውን የፍጥነት ወሰን በመተላለፍ ባለሞተር ተሽከርካሪን በማንኛውም መንገድ ላይ ማሽከርከር የተከለከለ ነው፡

## PART TWO

## SPEED LIMIT

### 5. General Precautionary Principles

1/ No driver shall drive a motor vehicle on any road in Ethiopia at a speed greater than that justified by law reasonable concern for all relevant conditions affecting the reasonableness of the speed at which the motor vehicle may be driven in safety; and such conditions shall include, without limitation, the following:

a) The surface, width and general conditions of the road;

b) The terrain through which the road passes, and the number of curves and inclines necessitated thereby;

c) The existence of precipitation, fog, night trip or other natural phenomena affecting visibility or traction;

d) The density of surrounding population;

e) The density of traffic, actually or reasonably to be expected on the road;

f) The existence of detours, blockades, stalled vehicles, fallen rock or other obstacles to passage; and

g) Any other circumstance adverse to the driver's ability to maintain full control over the vehicle at all times and to proceed in a safe manner;

2/ without prejudice to the provisions of Sub-Article (1) of this Article, no driver shall drive a motor vehicle on any road in excess of the speed limit stipulated under Articles 6, 7 or 8 of this Regulation;

Scanned by CamScanner

፫/ ማንኛውም አሽከርካሪ በማንኛውም መንገድ ላይ ባለሞተር ተሽከርካሪን በሚያሽከረክርበት ጊዜ ድንገተኛ አደጋን ለማስቀረት ካልሆነ በስተቀር የትራፊክ እንቅስቀሴን በሚያግድ አዝጋሚ ፍጥነት ወይም ለመንገዱ ከተቀመጠው ዝቅተኛ የፍጥነት ወሰን በታች መንዳት ወይም ፍጥነቱን በድንገት መቀነስ የለበትም፡

3/ No driver shall drive a motor vehicle at such slow speed as to impede the normal and reasonable movement of traffic or break the speed abruptly unless it is in response to an imminent danger;

፬/ ማንኛውም አሽከርካሪ ፍጥነቱን በድንገት ለመቀነስ የሚያስገድደው ሁኔታ ከተፈጠረ ይህን ሃሳቡን ጊዜውን በጠበቀና ግልጽ በሆነ ምልክት ማሳወቅ አለበት፣

4/ Any driver faced with a condition that compels him to abruptly slow down his speed, he shall give clear and timely signal of his intention of slowing down;

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሰረት አደጋ እንዳይደርስ በዝግታ ማሽከርከር አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ በአጠገቡ ከሚንቀሳቀስ ትራፊክ ጋር ሲነጻጸር በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች የፍጥነት ወሰን ውስጥ ሆኖ በዝግታ የሚነዳ ማንኛውም አሽከርካሪ የመንገዱን የቀኝ ጠርዝ ይዞ መሄድ አለበት፤

5/ Where reducing speed is necessary for safe operation as stated under Sub-Article (1) of this Article or when driving slowly as compared to other traffics moving nearby, any driver shall drive at the extreme right edge of the road;

፮/ በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር ፪፻፰/፪ሺ፫ እና በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ /እንደተሻሻለው/ ቁ. ፫፻፺፭/፪ሺ፱ ድንጋጌዎች መሰረት የአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪዎችን ለማስቀደም ሲባል ማንኛውም አሽከርካሪ ፍጥነቱን ከተፈቀደው በታች መቀነስ ወይም ማቆም ይኖርበታል፡፡

6/ Any driver shall slow down his speed below the permitted minimum speed limit or stop the motor vehicle where priority to emergency service vehicles shall be given as provided under Road Transport Traffic Control Regulation No 208/2011 and Road Transport Traffic Control Regulation No. 395/2017 (as amended).

## ፮. <u>ከከተማ ክልል ውጪ በጠቅላላ የተፈቀደ የፍጥነት ወሰን</u>

ማናቸውም አሽከርካሪ ከከተማ ክልል ውጪ፡-

፩/ የግል ተሽከርካሪን ቀጥሎ ከተመለከተው የፍጥነት ወሰን በላይ ማሽከርከር የተከለከለ ነው፡-

ሀ) በደረጃ አንድ መንገድ ላይ በሰዓት አንድ መቶ ሃያ /፩፻፳/ ኪሎ ሜትር፤

## 6. <u>General Speed Limit Outside Municipal Boundaries</u>

Outside the boundaries of Municipalities, no driver:

1/ Shall drive a private motor vehicle at a speed in excess of the following limits፡

a) In level one road 120 /One Hundred Twenty/ k. m per hour;

Scanned by CamScanner

ለ) በደረጃ ሁለት መንገድ ላይ በሰዓት አንድ መቶ /፩፻/ ኪሎ ሜትር፣

ሐ) በደረጃ ሶስት መንገድ ላይ በሰዓት ሰማንያ አምስት /፹፭/ ኪሎ ሜትር

መ) በደረጃ አራት መንገድ ላይ በሰዓት ሰባ /፸/ ኪሎ ሜትር፣

ሠ) በደረጃ አምስት መንገድ ላይ በሰዓት ስልሳ አምስት /፷፭/ ኪሎ ሜትር፤

ረ) በደረጃ ስድስት መንገድ ላይ በሰዓት ሃምሣ አምስት /፶፭/ ኪሎ ሜትር፤

ሰ) በደረጃ ሰባት መንገድ ላይ በሰዓት አርባ አምስት /፵፭/ ኪሎ ሜትር፤

ሸ) በደረጃ ስምንት መንገድ ላይ በሰዓት አርባ /፵/ ኪሎ ሜትር፡፡

፪/ የንግድ ተሽከርካሪን ቀጥሎ ከተመለከተው የፍጥነት ወሰን በላይ ማሽከርከር የተከለከለ ነው፡-

ሀ) በደረጃ አንድ መንገድ ላይ በሰዓት ዘጠና /፺/ ኪሎ ሜትር፤

ለ) በደረጃ ሁለት መንገድ ላይ በሰዓት ሰማንያ /፹/ ኪሎ ሜትር፤

ሐ) በደረጃ ሶስት መንገድ ላይ በሰዓት ሰባ አምስት /፸፭/ ኪሎ ሜትር፤

መ) በደረጃ አራት መንገድ ላይ በሰዓት ስልሳ አምስት /፷፭/ ኪሎ ሜትር፤

ሠ) በደረጃ አምስት መንገድ ላይ በሰዓት ሃምሳ አምስት /፶፭/ ኪሎ ሜትር፤

ረ) በደረጃ ስድስት መንገድ ላይ በሰዓት አርባ አምስት /፵፭/ ኪሎ ሜትር፤

ሰ) በደረጃ ሰባት መንገድ ላይ በሰዓት አርባ /፵/ ኪሎ ሜትር፤

ሸ) በደረጃ ስምንት መንገድ ላይ በሰዓት ሠላሣ /፴/ ኪሎ ሜትር፡፡

b) In level two road 100 /One Hundred/ k. m per hour;

c) In level three road 85 /Eighty Five/ k. m per hour;

d) In level four road 70 /Seventy/ k. m per hour;

e) In level five road 65 /Sixty Five/ k. m per hour;

f) In level six road 55 /Fifty Five/ k. m per hour;

g) In level seven road 45 /Forty Five/ k. m per hour;

h) In level eight road 40 /Forty/ k. m. per hour.

2/ Shall drive a commercial vehicle at a speed in excess of the following limits.

a) In level one road 90 /Ninety/ k. m per hour;

b) In level two road 80 /Eighty/ k. m per hour;

c) In level three road 75 /Seventy Five/ k. m per hour;

d) In level four 65 /Sixty Five/ k. m per hour;

e) In level five road 55 /Fifty Five/ k. m per hour;

f) In level six road 45 /Forty Five/ k. m per hour;

g) In level seven road 40 /Forty/ k. m per hour;

h) In level eight road 30 /Thirty/ k. m. per hour.

Scanned by CamScanner

፯/ **<u>በከተማ ክልል ውስጥ በጠቅላላ የተፈቀደ የፍጥነት ወሰን</u>**

ለማናቸውም አሽከርካሪ በከተማ ክልል ውስጥ ቀጥሎ ከተመለከተው የፍጥነት ወሰን በላይ ማሽከርከር የተከለከለ ነው፡-

፩/ የግል አቶሞቢል ወይም ሞተር ሳይክል ከሆነ፡-

ሀ) በቀለበት መንገድ በውስጠኛው መንገድ በሰዓት ሰማንያ /፹/ ኪሎ ሜትር፣ በውጭኛው በኩል በሰዓት ስልሣ /፷/ ኪሎ ሜትር፣

ለ) በዋና የከተማ መንገድ ላይ በሰዓት ስልሣ /፷/ ኪሎ ሜትር፣

ሐ) በመለስተኛ የከተማ መንገድ ላይ በሰዓት አርባ አምስት /፵፭/ ኪሎ ሜትር፣

መ) የሰፈር መንገድ ሆኖ የእግረኛ መንገድ ባለው መንገድ ላይ በሰዓት ሠላሳ /፴/ ኪሎ ሜትር፣

ሠ) የሰፈር መንገድ ሆኖ የእግረኛ መንገድ በሌለው መንገድ ላይ በሰዓት ሃያ /፳/ ኪሎ ሜትር፡፡

፪/ ከነጭነቱ በህግ የተፈቀደው ጠቅላላ ክብደቱ ከ፫ሺ.፭፻ /ሦስት ሺህ አምስት መቶ/ ኪሎ ግራም የማይበልጥ የንግድ ወይም የኪራይ ተሽከርካሪ ከሆነ፡-

ሀ) በቀለበት መንገድ በውስጠኛው መንገድ በሰዓት ስልሣ /፷/ ኪሎ ሜትር፣ በውጭኛው በኩል በሰዓት አርባ አምስት /፵፭/ ኪሎ ሜትር፣

ለ) በዋና የከተማ መንገድ ላይ በሰዓት አርባ /፵/ ኪሎ ሜትር፣

ሐ) በመለስተኛ የከተማ መንገድ ላይ በሰዓት ሠላሳ /፴/ ኪሎ ሜትር፣

መ) የሰፈር መንገድ ሆኖ የእግረኛ መንገድ ባለው መንገድ ላይ በሰዓት ሃያ አምስት /፳፭/ ኪሎ ሜትር፣

7. **<u>General Speed Limits within Municipal Boundaries</u>**

Within the boundaries of Municipalities, no driver shall drive a motor vehicle in excess of the following limits:

1/ Private Motor Car or Motorcycle:

a) In Ring Road in the inner lane 80 /Eighty/ k. m per hour; and in the outside lane 60 /Sixty/ k. m per hour;

b) In Main Municipal Road 60 /Sixty/ k. m per hour;

c) In Medium Municipal Road 45 /Forty Five/ k. m per hour;

d) In Local road with pedestrian walk way 30 /Thirty/ k. m per hour;

e) In Local road without pedestrian walk way 20/Twenty/ k. m per hour.

2/ Commercial Vehicle with a Permitted Maximum Loaded Weight Not Exceeding 3,500 /Three Thousand Five Hundred/ kilo gram or a rental Vehicle:

a) In Ring Road in the inner lane 60 /Sixty/ k. m per hour; and in the outside lane 45 /Forty Five/ k. m per hour;

b) In Main Municipal Road 40 /Forty/ k. m per hour;

c) In Medium Municipal Road 30 /Thirty/ k. m per hour;

d) In Local road with pedestrian walk way 25 /Twenty Five/ k. m per hour;

Scanned by CamScanner

ሠ) የሰፈር መንገድ ሆኖ የእግረኛ መንገድ በሌለው መንገድ ላይ በሰዓት ሃያ /፳/ ኪሎ ሜትር፡፡

፫/ ከንጭነቱ በሕግ የተፈቀደው ጠቅላላ ክብደቱ ከ፫ሺ፭፻/ሦስት ሺህ አምስት መቶ/ ኪሎ ግራም የሚበልጥ የንግድ ተሽከርካሪ፣ ባለሞተር ተሽከርካሪ ከነተሳቢ፣ ከባድ ካሚዮንና ግማሽ ተሳቢ፣ የእርሻ መሣሪያ ወይም ሌላ መሰል ተሽከርካሪ ከሆነ፡-

ሀ) በቀለበት መንገድ በውስጠኛው መንገድ በሰዓት አርባ /፵/ ኪሎ ሜትር፣ በውጭኛው በኩል በሰዓት ሠላሣ /፴/ ኪሎ ሜትር፣

ለ) በዋና የከተማ መንገድ ላይ በሰዓት ሃያ አምስት /፳፭/ ኪሎ ሜትር፣

ሐ) በመለስተኛ የከተማ መንገድ ላይ በሰዓት ሃያ /፳/ ኪሎ ሜትር፣

መ) የሰፈር መንገድ ሆኖ የእግረኛ መንገድ ቢኖረውም ባይኖረውም በዚህ መንገድ መጓዝ አይፈቀድለትም፡፡

**፰/ ልዩ የፍጥነት ወሰን**

፩/ በየጊዜው በመንገድ ላይ ያለውን የትራፊክ ፍሰት ወይም የትራፊክ አደጋ ሁኔታ በማጥናት ወይም ለህዝብ ደህንነት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ሚኒስትሩ ወይም አግባብነት ያለው አካል በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ እና ፯ ከተደነገገው የፍጥነት ወሰን ያነሰ የፍጥነት ወሰን ለተወሰኑ ወይም ለሁሉም ዓይነት ሞተር ተሽከርካሪዎች በአንድ የተለየ መንገድ ወይም የመንገድ ክፍል ላይ ወይም በተለየ ድልድይ ላይ ሊወስን ይችላል፣

፪/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ እና ፯ የተደነገገው ከፍተኛ የፍጥነት ወሰን ቢኖርም በትምህርት ቤቶች አካባቢ ለማንኛውም ባለሞተር ተሽከርካሪ ከፍተኛው የፍጥነት ወሰን በሰዓት ሰላሣ /፴/ ኪሎ ሜትር ነው፣

e) In Local road without pedestrian walk way 20 /Twenty/ k. m per hour.

3/ Commercial Vehicle with a Permitted Maximum Loaded Weight greater than 3,500 /Three Thousand Five Hundred/ kilo gram, a Combination Motor Vehicle and Trailer, a Combination Truck-tractor and Semi-Trailer, an Implement of Husbandry or other similar vehicle:

a) In Ring Road in the inner lane 40 /Forty/ k. m per hour; and in the outside lane 30 /Thirty/ k. m per hour;

b) In Main Municipal Road 25 /Twenty Five/ k. m per hour;

c) In Medium Municipal Road 20 /Twenty/ k. m per hour;

d) In Local road with or without pedestrian walk way, not permitted.

**8. Special Speed Limit**

1/ The Ministry or the concerned organ may, based on assessments on traffic volume or accident situations or in all circumstances where public safety so requires, reduce the speed limit prescribed under Articles 6 and 7 of this Regulation for any or all classes of motor vehicles travelling on any particular road or part thereof, or over any particular bridge;

2/ Notwithstanding to the provisions of Articles 6 and 7 of this Regulation, the maximum speed limit for any motor vehicle around school areas shall not exceed 30 /Thirty/ k. m. per hour.

Scanned by CamScanner

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሰረት የሚመደበው ልዩ የፍጥነት ወሰን ማስታወቂያው በግልጽ በሚታይ ስፍራ በየመንገዱ ወይም በየድልድዩ ላይ መደረግ አለበት፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፫) እንደተጠበቀ ሆኖ የመንገድ ምልክቶችን ለመትከል በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል አስፈላጊ የሆኑትን የመንገድ ምልክቶች ይተክላል፡

፭/ የፍጥነት መንገድን እንዲያስተዳድር በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል አስቀድሞ ለሚኒስቴሩ በማሳወቅ በሚያስተዳድረው መንገድ ላይ ምልክቶችን በመትከል ዝቅተኛ የፍጥነት ወሰኖችን ለማስቀመጥ ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፱. የማስፈጸም ስልጣን

ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው አካል ይህንን ደንብ በአግባቡ ስራ ላይ ለማዋል ክትትል እንዲያደርግ በዚህ ደንብ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

### ፲. የተሻረ ህግ

የባለሞተር ተሽከርካሪዎች ፍጥነት ወሰን የህግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፷፩ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

### ፲፩. ቅጣት

የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ተላልፎ የተገኘ ሰው በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር ፪፻፰/፪ሺ፫ እና በመንገድ ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ /እንደተሻሻለው/ ቁጥር ፫፻፺፭/፪ሺ፱ መሠረት ይቀጣል፡፡

3/ Notice of the special speed limit prescribed as per Sub-Article (1) of this Article shall be posted on regular intervals on the roads or bridges affected thereby.

4/ without prejudice to the provisions of sub article (3) of this article The concerned organ shall also install road signs appropriate to distinguish the speed limit designations;

5/ The body authorized to administer express ways may post road signs indicating the minimum speed limit prescribed on the express ways upon prior notice to the Ministry.

## PART THREE
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 9. Prerogative

The Ministry and the appropriate organ shall be responsible for the proper implementation of this Regulation.

### 10. Repealed Laws

Speed Limits Legal Notice No. 361/1969 is hereby repealed.

### 11. Penalty

Any person found in violation of the provisions of this Regulation shall be penalized as per the appropriate provisions of the Road Transport Traffic Control Regulation No. 208/2011 and Road Transport Traffic Control Regulation No. 395/2017 (as amended).

Scanned by CamScanner

**፲፪. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ የካቲት ፴ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም**

**ዐቢይ አህመድ (ዶ/ር)**
**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**12. Effective Date**

This Regulation shall enter into force as of the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 9th day of March 2022**

**ABIY AHMED /Dr./**
**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

Scanned by CamScanner